# አዲስ ኪዳን

VOLUME 2



ፓ/ር ዶ/ር ተስፋዬ ዘለቀ ተሰማ

የአዲስ ኪዳን ቤ/ክ የሙሉ ጊዜ

አገልጋይ

አዲስ ኪዳን ወንጌላዊት ቤ/ክ

## የሁለተኛ ዓመት ክብረ በዓል ልዩ ዕትም

**እሁድ 10:30am- 12:30 pm,**

**ማክሰኞ 7:00pm - 9:00 pm**

**745 Buchanan Street ,**

**San Francisco CA 94102**

**January 5,2014**

# አዲስ ኪዳን እትም 2


**የመፅሔቱ ዋና አዘጋጅ**

መስፍን ጉረሙ አያሌው

**ረዳት አዘጋጅ**

ኢዮብ አበበ

**የመጽሔት ዲዛይን እና ፅሁፍ**

እናትዓለም ኤጀርሳ

**ኤዲቶሪያል ቦርድ**

ፓስተር ዶ/ር ተስፋዬ ዘለቀ

ዶ/ር መዓዛ ክርስቶስ መኩሪያ



በአዲስ ኪዳን ቤ/ክ የሚታተም

# ማውጫ


መግቢያ ______________________________ 4

ርዕሰ መጽሔት ______________________________ 5

መልዕክት ______________________________ 6

ከእስልምና ወደ ክርስትና ______________________________ 7

ከግጥም ማህደር ______________________________ 9

አገልጋይና አግልግሎቱ ______________________________ 11

ቃለ ምልልስ ______________________________ 14

ከአገልግሎት ዘርፍ ______________________________ 17

እግረመንገድ ______________________________ 19

እንግዳችን ______________________________ 21

# መግቢያ

አዲስ ኪዳን መፅሔት አመታዊ እትም ይዛ ብቅ ብላለች ።

መፅሔቷ ብዙ መንፈሳዊ ቁምነገሮች የያዘች ስትሆን የግጥም ማህደር፣ አስተማሪ የሆኑ ቃለ ምልልስ፣ አካታለች።

አዲስ ኪዳን መፅሔት በመንፈሳዊ ዙርያ የምታጠነጥን ስትሆን ዕትሟ በየአመቱ ብትመጣም እንደ አስፈላጊነቱ በስድስት ወር በልዩ እትም ልትወጣ ትችላለች።

በዚህ አመታዊ መፅሔት ላይ ስለ አግልጎሎትና አገልጋይ በሚል የቀረበው ጽህፍ ላይ በርካታ ጥቅሶችን ከይዘቱ ጋር አብሮ እንዲነበብ አቅርባለች። ስለዚህም አንባቢ እያመሳከረ እንዲያነብ አዘጋጁ ይጠይቃል ያበረታታል።

በመፅሔቱ የግጥም ማህደር ቀልድን ለማዋዛት ተሞክሮአል። ርዕሰ መፅሔቷም የክርስትያን ሥነ ምግበርን ለመግለፅ ሞክራለች አመታዊ መልዕክትም አላት።

መልካም ንባብ።

## ርዕሰ መፅሔት

### የበደል ማርከሻ ይቅርታ ነው።

ከእናንተ እያንዳዱ ወንድሙን ከልብ ይቅር ካላለ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል ይላል ማቴ. 18፥35.

የክርስቲያን ሥነ ምግባር ኢየሱስ ነው፤ "እንግዲህ እንደ ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ ምህረት ርህራሄ ቼርነት ትህትና የዋህነት ትዕግስት ልበሱ እርስ በራሳችሁ ትዕግስት አድርጉ ማንም ባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ ክርቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ"። ቆላስያስ 3፣ 12-13. በዮሐንስ 15፣12 እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በራሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትዕዛዜ ይህች ናት በማለት በእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ አበከሮ ያስገነዝበናል። እንዲሁም በምሳሌ 19፣11 ሰውን ጠቢብ አዕምሮው ከቁጣ ያዘገየዋል ለበደለኛው ይቅር ይል ዘንድ ክብር ይሆንለታል።

ይቅርታ መሠረታችን ይቅር መባባላችን ነው ምህረት ለማግኘት ምህረት ማድረግ አለብን። ይቅርታ ማድረግ ያቃተው ሰው ይጎዳል ይቅርታ አለማድረግ በተጎጅነት ስሜት ውስጥ መኖር ነው። ይቅርታ የሰውን ልብ በፍቅር ወጥመድ ለመጣል አይነተኛ መሳርያ ነው። ያለፈን ነገር በመተው በመርሳት መኖር ይገባል። በዕብራውያን 10፣17 በደልህን አላየውም ደግሜም አላስበውም ብሎአልና ነገርን መከታተል ፅድቅ አይደለም ልብን ማነፅ ይገባል ክርስትና ዋጋ ቢያስከፍልም እጥፍ ክብር ደግሞ አለው።

አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስታትያን በመቻቻል በፍቅር በመዋደድ በይቅርታ ልብ መኖርን በፅኑ የምታምን ስትሆን ዘፍጥረት 45-1 ላይ ያለውን የዮሴፍን ታሪክ እንድታነቡ በመጋበዝ ርዕሰ መጽሔቷን ትቋጫለች።

## ልዩ መልዕክት፦ከቤተ ክርስትያኗ መጋቢ

## “እግዚአብሔር ነው”

ይህን ያደረገ **“እግዚአብሔር ነው፤”** ። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮርንጦስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ምዕራፍ ሦስት ላይ ስለቤተ ክርስትያንን አመሰራረትና አስተዳደግ ሲገልጽ **“እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር”** በማለት ጽፏል።

በሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ለተቋቋመችው አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስትያን መሠረትዋ በየሳምንቱ ማክሰኞ ማታ ለረጅም ዓመታት ይካሄድ የነበረ የቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ሕብረት ነው። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ህብረት ለረጅም ዓመታት ለብዙ ቅዱሳን በረከት በመሆን እንዲሁም ወንጌልን ላልሰሙ ደግሞ የወንጌል ድምጽ ሆኖ አገልግለዋል። አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስትያን አሁን ወደ ደረሰችበት ተቋም እንድትደርስ ሌላው ምክንያት ደግሞ የዛሬ ሁለት ዓመት ጀምሮ በርከት ያሉ ቅዱሳን በጸሎት፣ በቃል እንዲሁም በፍቅር በመዝራት፣ በመትከልና በማጠጣት በመድከማቸውም ጭምር ነው። ስለዚህም ብዙ ዋጋ እየከፈሉ የደከሙትን እያመሰገንኩ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በጽሁፉ “... **እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል”** እንደሚል ለእነዚህ በወንጌል ብዙ ለደከሙ ቅዱሳን በዝቶ ከሚትረፈረፈው በረከቱ እግዚአብሔር እንደያጠግባቸው እጸልያለሁ።

ስለተሰራው ሥራ ዋጋ የከፈሉትንና በብዙ የደከሙትን ካመሰግንኩ በኋላ፤ በዓመታት ውስጥ ለተሰራው የወንጌል ሥራና በቤተክርስትያን ደረጃ ተመስርቶ እየተካሄደ ስላለው በአሁኑ ወቅት ስለሚታየው ሥራ፣ **“ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ነው”** እላለሁ። ለሰዎች ራዕይን ጸጋንና ትጋትን በመስጠት የቤት ውስጥ ህብረት የነበረችውን በማሳደግ ቤተ ክርስትያን ወደ መሆን ያመጣ እግዚአብሔር ነውና ክብርና ምስጋና ሁሉ ለእርሱ ይሁን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ **“እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤”** ካለ በኋላ **“እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም”** እንደሚል ክብሩንና ምስጋናውን ሁሉ ለእርሱ እሰጣለሁ።

እንግዲህ ይህ ክብረ በዓል የአዲስ ኪዳን ቤተክርስትያን ምዕመን የእሁድ ጥዋት አምልኮ የጀመሩበትን ሁለተኛ ዓመት የሚያከብሩበት ነው። የመጀመሪያ እሁድ አምልኮ የተካሄደው ጃንዋሪ 8 እሁድ ቀን ሲሆን ስፍራውም 751 Webster Street San Francisco, CA 94117 ነበረ። ታዲያ ጃንዋሪ 8, 2012 የነበረው ዝግጅት እንደዚህ እንደ አሁኑ የደመቀ አልነበረም። ጅማሬዋ ታናሽ ሲሆን በጣም አነስተኛ በሆነች ቤት ውስጥ በብዙ ፍርሃትና ጥንቃቄ እንደነበረ አስታውሳለሁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ በዚህ መልክ ቤተ ክርስትያኒቷ ተደራጅታ ለእግዚአብሔር ህዝብና ለከተማው እንዲህ በረከት ሆና ሳይ እደነቃለሁ። ይህም ገና ሊመጣ ላለው ብዙ የእግዚአብሔር በረከት እንደምልክት ሆኖ ተስፋ ይሰጠኛል። ጅማሬዋ ምንም ታናሽ ቢሆንም ፍጻሜው ከእግዚአብሔር ጋር ታላቅ እንደሚሆንና ለብዙዎች መጠለያ እንደምትሆን ትልቅ እምነት አለኝ።

ለዚህ ክብረበዓል ተካፋዮች ለሆናችሁትና ይህችን መጽሔት ለምታነቡ ሁሉ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስትያን እግዚአብሔር ለተከላት ዓላማ ታማኝ በመሆን ያሰበላትን ሁሉ እንድትወርስ በጸሎታችሁ እንድትደግፉን በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ፓስተር ተስፋዬ ዘለቀ ተሰማ PhD

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስትያን ሙሉ ጊዜ አገልጋይ

# ከእስልምና ወደ ክርስትና

ፈትህያ ከድር ጀማል እባላለሁ ከእናቴ ከወ/ሮ ሩቅያ የሱፍ ከአባቴ ከአቶ ከድር ጀማል በአዲስ አበባ ተወለድኩ። ዕድሜዬም ለትምህርት ሲደርስ በቤት ውስጥ ውስታዝ (አስተማሪ) እየመጣ ቁራን ቀረቼ ነው ያደኩት። በአንዋር መስጊድም ሀዲስ (ስብከት) ተከታትያለሁ፤ በሙስሊም ደንብም ሰኞና ሐሙስ እጾም ነበር የረመዳ ጾምም እጾማለሁ በእንዲህ ሁኔታ ነው እድገቴ::

ከእስልምና ቤተሰብም የተገኘሁ በመሆኔ እስልምናውን አጠብቃለሁ፣ አምስት እርከአት እሰግድ ነበር ከስግደቴም ብዛት የተነሳ ግንባሬ ጠቁሮአል በእስልምና ኑር (ብርሃን) ተብሎ ይታመናል። ዕድሜዬ 19 ዓመት ሲሆነኝ ወደ ሳውዲ አረቢያ ሔድኩ መካ (ለዚያራ) ሔጄአለሁ ጅዳም ተመልሼ አንድ ዓመት ከሶስት ወር ቆየሁ ከዛም በሪያድ ስምንት ወር ተቀመጥሁ::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ የአንድ ነጭ ሚስት የሆነች አንዲት አበሻ እታፈራሁ የምትባል ወደ ጅዳ ለእረፍት ከነቤተሰቧ ለመሄድ ትኬት ቆርጣ ለጉዞ በዝግጅት ላይ እያለች ትታመማለች በህመሟም ምክንያት ጉዞዋን ትሰርዛለች ይህችም እህት የሚረዳት ሰው ትፈልግ ነበር፡: በአንድ አረብ ቤትም በምሰራበት ጊዜ አንድ አበሻ አገኘሁ ከሷም ጋር ተቀራርበን እንጫወት ነበር:: ይህችም ሀበሻ የአውልያ መንፈስ የነበራት ነበረች እኔም ስለ ቤተሰቤ ኑሮ ማግኘትና ማጣት ነግሬአት ነበርና ለአውልያው በትገብሩት እኮ ወደ ቀድሞው ንብረታችሁ ትመለሱ ነበር ትለኝ ነበር:: አንቺም ብትካድሚው ይሆንልሻል እያለች ታበረታታኛለች:: እኔም በመስማማት እንዳለችኝ ቡና እያፈላሁ ሥርአቱን ሁሉ እፈፅም ነበር:: በእንዲህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ህልም ዓየሁ ህልሙም ቢጫ መጋረጃ ሲጋረድ ነበር ይህንኑ ህልሜን ለዚች አውሊያ መንፈስ ለአለባት እህቴ ነገርኳት።

እሷም ህልሙን በሚገርም ሁኔታ ፈታችው እንዲህም አለች አንቺን የሚጋርድ የሚከታተል የክርስትና መንፈስ አለ:: አንቺ በቃ ትለወጫለሽ ክርስቲያን ነው የምትሆኚው አልችኝ:: እኔም ቆጣ ባለ ድምጽ ክርስቲያንማ አልሆንም አልሆንም አልኳት:: የሚገርመው እንዲህ ካልኩ በኋላ ነው እንግዳ ነገር በሕይወቴ የሆነው።

የነጭ ሚስት የሆነችው እህት እታፈራሁ ጋር ልመልሳችሁ አንድ ወንድም ወደ እኔ መጥቶ አንድ አበሻ አለች እርሷም እታፈራሁ ትባላለች:: ታማ ነው ያለችው የሚረዳት ሀባሻ እህት ትፈልጋለችና አንቺ ብትረጃት አለኝ እኔም ምንም ሳላቅማማ ለጥያቄው ተስማማሁና ወሰደኝ :: እቤቷም ስደርስ ታማ የነበረችው የፈረንጁ ሚስት እታፈራሁ ከመኝታዋ ተነስታ አስተናገደችኝ:: ባሏም ነበረና በመገረም አማርኛ ናፍቆሽ ነበር እንዴ ህመሙ የተወሽ በማለት ቀለደ፡ ይህችም እህት ለካ ክርስቲያን ነበረች:: በእኔ መምጣትም በጤንነቷ ላይ አዲስ ነገር እንድሆነ ታወቀኝ።

በዚች እህት ቤትም ስገባ ለደሞዝ አልነበረም እሷን ለመርዳት እንጂ ይሁንና በወቅቱ ሥራ አልነበረኝም ቢሆንም ከእርሷ ጋር ያለኝ ጊዜ ጥሩ ነበር:: በዚህ ቤትም ሥኖር መዝሙር እሰማለሁ በአንድ ወቅት እናቴ ስልክ ደወለችልኝ:: የደወለችልኝም የምወደው አባቴ ታሞ ስለነበር እባክሽ በእምነትሽ ፀልይ አለችኝ:: በአባቴ መታመምም በጣም ደነገጥኩ:: አባቴንም እወድ ስለነበር ግራ ተጋባሁ የአባቴንም መታመም ለእታፈራሁ ነገርኳት:: እታፈራሁም አይዞሽ እፀልያለሁ አለችኝ:: እርሷም እፀልያለሁ ስትለኝ በውስጤ ደስታ ተሰማኝ:: የአባቴንም ስም ነገርኳት:: ስሙንም እየጠራች የዘር ማንዘር የአውልያ መንፈስ እያለች በመቃወም ትፀልይ ጀመር:: እኔም አብሬ ከእርሷ ጋር እንድፀልይ የሚል መንፈስ ውስጤን ያነሳሳው ጀመር:: ልታገስም አልቻልኩም ተነስቼም ወደ መኝታ ቤቷ ሄድኩና በሯን ለማንኳኳት እያመነታሁ መኝታ ቤቷ በርጋ ቆሜ እየገሠፀች ስትፀልይ አዳምጣት ነበር:: በፀሎቷም ተገረምኩ ከፍ ባለ ድምጽ የአባቴን ስም እየጠራች ስትፀልይ እንዲህም ያለ ሰው አለ እንዴ ለሰው ግድ ብሎት አምላኩን የሚለምን ብዬ ትንሽ አዳመጥኳትና በሯን አንኳኳሁ:: እታፈራሁም ፀሎቷን አቋርጣ በሩን ከፈተችልኝ ግን ደንገጥ ብላለች ይቅርታ አልኳትና ከአንቺ ጋር መፀለይ እፈልጋለሁ አልኳት:: ፈገግ አለችና ነይ ግቢ የምንፀልየው ግን በእኔ ፀሎት ነው አለችኝና አስቀድማ ለእኔ ፀልያ ንሥሀ አስገባችኝ በእኔ ላይ ያለውን የዘር ማንዘር መንፈስ መትታ ከፀሎቷ ጋር ተቀላቀልኩ እኔ ተንበርክኬ እያለሁ ትኩረት አድርጋ የምትቃወመው የመሐመድ መንፈስ እያልች ነበር:: በውስጤም ኃይለኛ ነገር ገብቶ ስለ ነበር በይ የምትለኝን ሁሉ እል ነበር:: ከእታፈራሁ ጋር ተስማምቼ ከፀልይኩ በኋላ ውስጤ በደስታ ተሞላ መፅሐፍ ቅዱስም ስጥታኝ ስለነበር አስታውሳለሁ ለ22 ቀን በተከታታይ

# ከእስልምና ...

አነበብኩ:: ከዚህ በኋላማ ምን ልንገራችሁ አንደኛ የወንጌል ሰባኪ ሆንኩ:: ለብዙ ሀበሾች ኢየሱስ ያድናል ማለት መመስከር ሥራዬ ሆነ:: እግዚአብሔርም ብዙ ነፍሳትን ምርኮ አድርጎ ይሰጠኛል።

የሚገርመው እናቴ ከእኔ በፊት ተደብቃ ክርስትያን ሆናልች የእናቴ የክርስትና አመጣጥም በህመም ሲሆን አጎቴም በጌታ ስልነበረ ለእናቴ ወደ ጌታ መምጣት ምክንያት እሱ እንደሆነ አውቃለሁ።

በዚህ አጭር የክርስትና አኗኗሬም ችግሮች ገጥመውኛል ወደ ክርስትና መምጣቴ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ተስምቶ ስለነበር ከድር የሚባል በሪያድ የቆንሲል ፀሐፊ ስልክ ደውሎ ይጠራኛል ጥሪውንም ተቀብዬ ወደ ቤቱ ሔድኩ  በቤት ውስጥ በርካታ ሴቶች ሒጃብ የጠመጠሙ ነበሩ ሁኔታቸውን ሳይ ለግዜው ደንገጥ ብልም ወዲያው ውስጤ በድፍረት ተሞላ እነሱም ያነሱልኝ ጥያቄ ሽሀድ (ንሰሀ) ግቢ የሚል ነበር እኔ ገን በድፍረት ኢየሱስን ሰበኩላቸው መጠነኛ ተግዳሮት ቢያጋጥመኝም የእግዚአብሔር ጥበቃ ከእኔ ጋር ስለ ነበረ አለፍኩት።

እንደሚታወቀው በአረብ አገር ክርስትና በድብቅ ነው የሚመለከው ጌታንም እንዳገኘሁ ወደ አማኞች ህብረት ተቀላቅያለሁ:: ይሁንና ቤተክርስትያኗን ወይም ፓስተሩን ሳላሳውቅ ለምስክርነት ወደ እስልምና አባቶች ምጥዋ ይባላሉ እሔድ ነበር በዚህ ወቅት አስታውሳለሁ ፓስተሬ አትሂጂ ለብቀላ አንቺን ተከታትለው በመምጣት በድብቅ ለምናመልከው ሁሉ ችግር ይሆንብናልና በጥበብ ተመላለሺ አለኝ።

እኔ ግን ክርስቶስ ውስጤ ገብቶ ስለነበር ወንጌልን አስብክ ነበር እግዚአብሔርም እኔን ተጠቅሞ ብዙ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያ ይጨመሩ ነበር ስልክም የሚደውሉልኝ በረከቱ፡

አንድ ቀን እንዲህ ሆነ አንድ የኦርቶዶክስ አማኝ ስልኬን ከሰው ወስዶ ደወለልኝና እቤቱ ጋበዘኝ:: እኔም መፅሐፍ ቅዱሴን ይዤ እቤቱ ሔድኩ:: እቤቱ ሰገባ አልኮል እየጠጣ አገኘሁት:: ገና ቁጭ ስል አንቺ ብሎ ሰባኪ እያለኝ መፀሐፍ ቅዱሱን ሊነጥቀኝ እየታገለ የዱላ ውርጅብኝ አወረደብኝ ክርስትና ስጀምር የደረሰብኝ ትልቅ ጉዳት ይህ ነበር ይሁንና በዚህም ሰአት እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነበር። በአካሌ ላይ ምንም ችግር አልደረሰብኝም ድብደባው ግን ለእኔ ከባድ ነበር፡፡

ጌታን በአገኘሁ በአንድ ዓመቴ ወደ አደስ አበባ ተመለስኩ ቤተሰቦቼም ጎረቤቶቼም ሙስሊሞች ናቸውና አንድ ቀን ጎረቤት ተጠርቼ ሄድኩ በተጠራሁበት ቤት ብዙ ሰዎች ነበሩ ውይይታቸውም አስደንጋጭ ነበር:: ጀሀድ አውጀን ክርስቲያኑን እንጨርስ የሚል ነው:: በእውነቱ በጣም ዘገነነኝ እራሴንም መደበቅ አልቻልኩም ክርስቲያን ምን አደረጋችሁ በማለት ድምጼን ከፍ አድርጌ እግዚአብሔር ይገስጻችሁ አልኳቸው ሁሉም ተደናገጡ የቤተሰቦቼ ቤትም ሀብተጊዮርጊስ አሜሪካ ጊቢ ነው:: በዛ አካባቢም እቃም ሲወድቅብኝ ቢያደናቅፈኝም በኢየሱስ ስም እል ነበር:: በዚህም በጣም ታወቅኩ:: ይሁንና ማንም እጁን አልሰነዘረብኝም የአናቴንም ክርስቲያን መሆን ይፋ ያደረኩት እኔው ነኝ።

አንባቢዎቼ መዳን በማንም የለም እንድንበት ዘንድ ከላይ የተሰጠን ስም ኢየሱስ ብቻ ነው:: ኢየሱስ እውነት መንገድ ህይወትም ነው:: ከኢየሱስ በቀር ወደ አብ የሚገባ የለም መንገዱ እሱ ነው። በፍፁም ልብ በፍፁም ሀሳብ በታማኝነት እግዚአብሔርን መከተል ይገባል እላለሁ። ጌታን ሳገኝ በረከቱ እየተከተለኝ ነው::  እግዚአብሔርም በትዳርና በልጅ ባረከኝ ፤   እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ጌታ እየሱስ ይባርካችሁ።

ፈትህያ ከድር

# ከግጥም ማህደር

**ትንሽ ዕድሜ ቀረው ራዕይ፡ 12፣7-12**

ሰማይ ጥርት ብላ ምድር ታወከች፡
ዘንዶው ሲመጣባት እየዬ እያለች
በሰማይ መላዕክቱ ስይፋቸውን መዘው
ወደ መሬት ጣሉት ዲያብሎስን ወግተው
ትንሽ ዕድሜ በምድር እንዳለችው አውቆ
የሰውን ጉሮሮ ተናንቆ ተናንቆ፣
ሲኦል ይዞ ሊሔድ ክፋቱን አምቆ
ሰውን ሰበሰበ በጉያው ደብቆ
ትንሽ ዕድሜ ቀረው
ጭካኔውን ይዞ ሊያበረው ሊያበረው።

**ድሙቴ/ለፈገግታ/**

ዘንድሮ ድሙቴን አይጢቱን ፈራቻት፡
ንፍት ብላ ቀረች ቦታ ባይመቻት፡
አይጧ ጨፈረች አሳይታ እስክስታ፡
ድሙቴ ዝም አለች እያየቻት ፈርታ፡
አይታ ተመልክታ መታገሷ ምነው፡
ልብሶቼን በሙሉ ስትቦጫጭቀው።
ተላምዳብኝ ይሆን? ነው ወይስ ፍራቻ?
ታዲያ ለምን ይሆን ቁጭ ያሉት ያለ አቻ?
እንዲህ ስታምሰው እልፍኙ ውስጥ ገብታ
ውርዬ ለምን ነው የመረጥሽ ዝምታ።

ከመስፍን ጉርሙ አያሌው፡

# ከግጥም ማህደር

## ጠቢበኛው ሊቁ

ጠቢበኛው ሊቁ ሲያሰላስል አድሮ-:
ደረስኩበት አለ ሁሉንም መርምሮ-:
የፍጥረትን ምስጢር ሊያበስር ተመክሮ::
አስፈላጊ አይደለም አለ ጠቢባቸው
ግራቭቲ ካለ የሚያሳስባቸው::
የሂግስ ቦስን ፓርቲክል ካለ መሃላቸው::

ስሙን ከፍ አድርገው "እግዜር ቁስ ይባላል ብለው ነገሯቸው:
ይህንን ሲሰሙ ሁሉም ደስ አላቸው
የምስጢሩን ፍች ያገኙ መስሏቸው::
ምድረ ኤትይስት ሁሉ በባዶ አለማቸው::
ሣይጠይቁ ማመን: ግራ ቢገባቸው::

ግራቭቲስ ቢሆን ከየት ነው የመጣው?
ከመጓተት በፊት ማን እርሱን ፈጠረው?
የሂግስ ቦሰን ፓርቲክል መሃል ማን አስገባው?
ወይስ ኳንተም ፊዚክስ ማተማቲክስ ነው?
የነዚህን ሕጉን ማን ደነገገው?
እስቲ ተናገሩ ምስጢሩ ምንድን ነው?

ማተማቲክስ ቢባል ቢደመር ቢቀነስ
ቢባዛ ደጋግሞ በነፎርየር ሲሪየስ
አንዲት ቁስ አይፈጥር አዕላፍ ቢያሰልስ::
ምስጢሩ ግልፅ ሆኖ ዝንተ ዐመት አለፈዋል:
ለጠቢባን ሸፍን: ሁኖባቸው ኑሯል::
ሰለ ጌታ ኢየሱስ ፍጥረት እውን ሁኗል::

በሱ ነው ስለ እሱ: ከሱ የተፈጠረው
መረጃው ኢየሱስ ሁሉን የጀመረው::

**ከወንድም ፋሲል ፈንቅሌ**

## አገልጋይና አገልግሎቱ

በመስፍን ጉርሙ ተዘጋጀ

አገልግሎትን ስናስብ አገልጋይ ሊረዳው የሚገባው ዋና ነገር ቢኖር ጥሪውን (ምርጫውን) ማወቅና የእግዚአብሔር ሥራ ለእግዚአብሔርና ለሰው ልጆች ጥቅም የሚውል መሆኑን ነው። ስለዚህም አገልጋይ የመሆናችን ዓላማ ለራሳችን የማይገባንን ክብር ለመውሰድና ዝናን ለማትረፍ ሳይሆን በየጊዜው ለጌታ ክብር የምንሰራ የንጉሡ ሠራተኞች መሆናችንን በማወቅ ሊሆን ይገባል። (ዘፀአት፡ 3፤7–10, ሉቃስ፡ 5፤10, ሐዋ. ሥራ 9፤15–16) ይህም ማለት ለጥሪው የምንሰጠው ምላሽ እግዚአብሔር ለፈለጋቸው ሥራ፣ (ለተጠሩበት ጥሪ) ማንነታቸውን እራሳቸውን በሚገባ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ለዚህ ጥሪ የሚሰጡት ምላሽ በድርጊቱ የተሟላ መሆን ስለሚገባው ነው። ለዚህ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው ዕዝራ በዕዝራ 7፤10 ላይ እንደምናናበው ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። ከዚህ በታች አንድ አገልጋይ የተሳካና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ ሊያደርግ የሚገባውን ነገሮች በመዘርዘር እንመለከታለን።

### 1.አገልግሎት ፈቃድን በመስጠት የሚገለፅ ነው።

በሐዋ ሥራ 9፡ 6 ላይ ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያው ጳውሎስን በሚያስደንቅ ብርሃን በተገናኘው ጊዜ ሐዋርያው ለጌታ ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ ጥሩ ምሳሌ ነው። ***”እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ። ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም። ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው።”*** ሐዋርያው ያለምንም ማንገራገር ለመጣለት ጥሪና ለተቀበለው መገልጥ ገደብን ሳያስቀምጥ በሙሉ ልቡ መስማማት ብቻ ሳይሆን ለጌታው ትዕዛዝ ራሱን ሰጠ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም የሐዋርያው ጳውሎስን ሙሉ መታዘዝ በሚሲኒዮናዊ አገልግሎቱ እንዴት ጌታውን እንዳገለገለና አብያተ ክርስትያናትን በዓለም ዙርያ እንደቋቋመ በመተረክ አስቀምጦልናል።

### 2ኛ. አገልግሎት መልካም ምሳሌነት ባለው ህይወት የሚገልጥ ነው፡

አገልጋይ ለጥሪው ጌታ ምላሽ ይሰጣል ብለን ስናስብ የሚሰጠው ምላሽ ወይም አገልግሎት በመልካምና ምሳሌ በሆነ ህይወት የተደገፈ መሆን ይገባዋል። በአገልጋይ ህይወት ውስጥ ዘወትር ሊያገኘው ሊመለከተው የሚገባውን ህይወት፡ (ኑሮ) ፍሬ በማፍራት ሊሆን ይገባል:: መልስ በመስጠት የጥሪውን ፍላጎት መፈፀም ማለት ነው። መልካም ምሳሌነት ያለው ህይወት በምን በምን ሊሆን ይገባል ስንል መታዘዝ ድራሻው ትልቅ ነው። የማይታዘዝ አገልጋይ የራሱን እንጂ የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሰራ አይችልም፤ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ማንነት ያለው አገልጋይ በዕቅድና በጌታ ፈቃድ ውስጥ ስለሚመላለስ ወደሚቀጥለው ደረጃ ይሻገራል። የሐዋ ሥራ 5 ፤ 29 ***እንደምናነበው “ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል”፣*** እንደሚል የአገልጋይ ትኩረቱና ትጋቱ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ህይወት ነው። ይህ ካልሆነ ባለመታዘዙ ዘወትር እራሱን የሚያገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላና ውስብስብ ችግር ውስጥ ሲገባ ነው። ሆኖም አገልጋይ ይህን የሚያደርገው ደግሞ በራሱ ችሎታም አይደለም። አገልጋይ በታማኝነት ጌታን ያገለግሉት ዘንድ ኃይልና ብቃት የሚያገኘው ታማኝ አድርጎ በመቁጠር ከጠራው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1 ጢሞቴዎስ 1፡ 12 ላይ ***“ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቈጠረኝ፥ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ፤”*** በማለት ይናገራል። ስለዚህ ዘወትር፡ ታማኝነት ለእግዚአብሔር ጥሪ መልስ የምንሰጥበት መንገድ እንደሆነ ልናውቅ ይገባናል።

### 3ኛ. ዓገልግሎት ምንድን ነው?

አገልግሎት ምንድነው ተብሎ ለሚጠየቅ ጥያቄ የምንሰጠው አጭርና ሙሉ መልስ፡ የመዳናችን አላማ ሚስጥሩ እግዚአብሔርን ማገልገል ነው የሚል መሆን አለበት። ይህን እውነት በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ተጽፎ እናገኛለን።

ዘጸዓት 19፡ 4፤ ***በግብፃውያን ያደረግሁትን፥ በንስርም ክንፍ እንደተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል። 5፤ አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፤ 6፤ እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ። ለእስራኤል ልጆች የምትነግራቸው ቃል ይህ ነው።*** ይህንኑ በመከተል በአዲስ ኪዳናችን ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ ላይ ይደግመዋል። 1 ጴጥሮስ 1፡ "***9 እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደንቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ 10 እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።***" ስለዚህም በክርስቶስ ያመነና የዳነ ሁሉ ካህን ብሎም አገልጋይ ነው። አገልግሎትም ለእግዚአብሔር መገዛታችን መግለጫ ምልክትና የፅድቅ ባርያ የመሆናችን መግለጫ ነው። በሌላ አነጋገር የክርስቶስ ባርያ መሆናችንን የሚታወቀው በአገልግሎታችን ነው። እንግዲያው ልብ እንበል አገልግሎት የእግዚአብሔር ሹመት ነው፤ ለዚህም ነው ጢሞቲዎስ ለአገልግሎት የሾመኝ ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረኝ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ በማለት በ1ኛ.ጢሞ 1፣ 12 የጻፈው።

**4ኛ. አገልጋይ አለምንና በአለም ያለውን ከማፍቀር መጠበቅ ይኖርበታል**

ሐዋርያው ዮሐንስ ሲጽፍ 1 ዮሐንስ 2፡ *"15-16 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። 17 ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።"* አገልጋይ ሐዋርያው እንደጻፈው በዓለም ካለው ከሥጋ አምሮትና ምኞትና እንዲሁም ከዓይን አምሮት ራሱን መጠበቅ ያስፈልገዋል። ከዚህ ጋር የሚያያዘው ለገንዘብ መገዛትም እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ ሌላ አምላክ ወደ ማምለክ የሚያመራ ስለሆነ ይህም ከአገልጋት አይጠበቅም። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ላይ ግልጽ በሆነ መልክ በዮሐንስ ወንጌል 6 ሲያስተምር *24 "ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም"* " ብሏል።

**5ኛ. አገልግሎት የሚያስከፍለው ዋጋ**

አገልግሎት በሰው ፈቃድ አይመችም በእግዚአብሔር መንፈስ ግን ይቻላል:: *መንፈሳዊ አገልግሎት በእግዚአብሔር ፀጋ* በእግዚአብሔር ስጦታ ብቻ ሲሆን እግዚአብሔር ችሎታን ሳይሆን የሚጠይቀን ፈቃዳችንን ነው:: አገልግሎትም የሚያስከፍለው ዋጋ አንድ ደቀ መዝሙሩ የሚያከፍለው ዋጋ ነው። ሉቃ. 9 ፣ 23 – 24 ተመልከት። ይህም ማለት አገልግሎት እራስን መካድን የሚጠይቅ ሲሆን ማለትም ክብርን ዝናን መተውም ማለት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለከፈለው ዋጋ ለፊሊጲሲዮስ ሰዎች የጻፈውን እንመልከት። ፊሊጵስዩስ 3 ፣ *4 እኔ ግን በሥጋ ደግሞ የምታመንበት አለኝ። ሌላ ሰው ማንም ቢሆን በሥጋ የሚታመንበት እንዳለው ቢመስለው፥ እኔ እበልጠዋለሁ። 5 በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ፥ ከእስራኤል ትውልድ፥ ከብንያም ወገን፥ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤ 6 ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ፤ በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ ነበርሁ። 7 ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ። 8-9 አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤ 10-11 እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ*

*እንድመስለው እመኛለሁ።"*

**6ኛ.አገልግሎት በፈቃደኝነት መቀበልን እራስን ከሁሉ ነገር የጠበቀ መሆን አለበት፡**

መንፈሳዊ አገልጋይ አገልግሎቱ ከቤቱ መጀመር አለበት በትህትና በፍቅር በርህራሄ በአክብሮት በትዕግስት በመቻቻል የኑሮ ምሥክር ሉሆን ይገባል። ይህም ማለት አገልጋይ እንደሚገባ ራሱን በማዘጋጀት ለሚያገለግላቸው ሰዎችና ለህብረተሰብ ሞዴል መሆን አለበት። በፊሊጵስዩስ 2 ፥ 5 – 9 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወልንን ምሳሌ በተግባር ለመለማመድ መትጋት ይጠበቅበታል።

ተጨማሪ ምሳሌ ካስፈለገ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈውን ተመልከት። “7 *ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትከባከብ፥ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፤ 8 እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና። 9 ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን። 10 በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን፥ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤ 11-12 ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም፥ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሆንን ታውቃላችሁና። 13 ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል ሳይሆን ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።”* 1ኛ. ተሰሎ 2፤ 7 – 13

**7ኛ.- የፀጋ ሥጦታዎችን ማጤን፤**

የእግዚአብሔር ሕዝብ የጸጋ ሥጦታን የተቀበለ እንደሆነ ሀዋርያው ጳውሎስ በ 1ኛ.ቆሮ. 12 ፥ 8 – 11፣ በ ሮሜ 12 ፥ 6 – 8 እና ኤፌ. 4፣ 11 ላይ በዝርዝር ጽፏል። ይህም የጸጋ ሥጦታ ለአማኞች ያከፋፈለው እግዚአብሔር እንደሆነ በመጥቀስ ጸጋቸውን አውቀው እንዲያገለግሉ አስተምሮአል። ወደ ሮሜ ሰዎች 12፡ 4 በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ 5 እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን። 6 እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ 7 አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ 8 የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።

የፀጋው ባለቤት እግዜር እንጂ ፀጋ በራሳችን ጥረት እደማይመጣ እና እግዚአብሔር በሚሰጠን ፀጋ እንዳንታበይ ለግላችን ሳይሆን ሰውን የምናተርፍበት የምናስመልጥበት ወዘት ነው። ስለዚህም ፀጋ የተሰጠበትን ምክንያት በማወቅና፡ አጠቃቀሙን በማወቅ ልናገለግል ይገባል። የምንሰጠው አገልግሎትም እንደ እግዚአብሔር ቃል መሆን ያለበት ሲሆን ከአገልግሎታችን በፊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅና መፀለይ ይገባል:: ይህ ሲሆን በአገልግሎታችን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለማክበር ይውላል።

**8 ) የእራስን ክብርና ሥልጣን መፈልግ ሥፍራን ያስለቅቃል - ቤቱን ትቶ እንደሚበር ወፍ ነው፤**

በመጨረሻም 2ኛ ሳሙኤል 15:1-6 ላይ የተጻፈው የአቤሴሎም አካሄድ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚጋፋ ስለሆነ ስፍራን የሚሰጥ እግዚአብሔር መሆኑን አውቀን እግዚአብሔርን እንጠብቅ እንጂ አንጋፋ:: እግዚአብሔር ባስቃመጠው የአገልግሎት ሥፍራ ያልተገኘ የሌላውንም አገልግሎት ያሰጥላል። በለዘበ አቀራረብ የሰውን ልብ እየሰረቁ የእግዚአብሔር ቤት የእራስን ዝና ለማትረፍ ፈጽሞ ሊሆን ስለማይገባ እግዚአብሔር ባለን ቦታ ብቻ የምንገኝ ካልሆነ ያልተሰጠውን ፈጎ እንደተንጠራራውና እንደተጣለው እንደሰይጣን እንዳንሆን ልንጠነቀቅ ይገባል። ሰያጣንን የሰሙት አዳምና ሔዋንም አትበሉ የተባለውን በመብላታቸው እንደ እግዚአብሔር ለማወቅ ብለው በመሳሳታቸው እነርሱም ወደቁ ለዓለምም ተረፉ ይህም ሥፍራቸውን ባለማወቃቸው ነው። የተከፈቱ አገልግሎቶች ሁሉ የእኛ አይደሉም አግልግሎት በምሪት እንጂ በምኞት አይደለም ክብርን ለመፈለግና ሥፍራን ለመፈለግ አንምጣ:: የአገልግሎት በሩ ትህትና ታማኝነት ነው።በጥቂት ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ ይላል፡ በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች እኩል ናቸው።

## ቃለ ምልልስ

## በአገልግሎት ዙሪያ ከእህት አበበች አሰፋ ጋር ቆይታ

አዲስ ኪዳን : ስም ማን ልበል?

አበበች/አቡ : አበበች አሰፋ::

አዲስ ኪዳን : ስለ አገልግሎትሽ ላነጋግርሽ ፈቃደኛ ነሽ?

አበበች/አቡ : በጣም ፈቃደኛ ነኝ::

አዲስ ኪዳን : በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስትጀምሪ ምን አይንት አገልግሎት ነው /በስም/ እስቲ ከእርሱ እንጀምር::

አበበች/አቡ : የጀመርኩት አገልግሎት የፍቅር ግብዣ (ኢጋፔ) ነው::

አዲስ ኪዳን : ስለ አገልግሎቱ ብታብራሪልኝ?

አበበች/አቡ : እንግዲህ አገልግሎቱ የፍቅር ግብዣ ነው:: ይህ አገልግሎት በስድስት ቡድን ተዘጋጅቷል; እኔም የአንዱ ቡድን ሃላፊ ስሆን የስድስቱም ህብረት መሪ ነኝ:: የእኔም ጉልህ ድርሻ የስድስቱም ቡድን መሪ መሆን ይመስለኛል::

አዲስ ኪዳን : የቡድኑ ስብጥሩ እንዴት ነው?

አበበች/አቡ : በአምስት ሴትና በአራት ወንድ ጥምሪት ነው::

አዲስ ኪዳን : ለዚህ አገልግሎት ያለሽን ስሜት እንዴት ትገልጭዋለሽ?

አበበች/አቡ : ይኼ አገልግሎት ለእኔ ትልቅ ነው; ለእራሴም ይገርመኛል:: እኔ ለእዚህ በቂ ነኝ ወይ እላለሁ:: እንግዲህ እግዚአብሔር ልቤን ወደዚህ ከመራው ስራው የእግዚአብሔር ነውና ደስተኛ ነኝ::

አዲስ ኪዳን : ይህ የፍቅር አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን ባለፈ ለአንቺ ምን ትርጉም አለው?

አበበች/አቡ : የዚህ የፍቅር ግብዣ አገልግሎት ለእኔ ልዩ ትርጉም አለው:: ይኸውም ቤተ ክርስቲያንን ማገልገሌ እግዚአብሔርን ማገልገል ስለሆነና ከወገኖችም ጋር ስለአስተዋወቀኝ ህብረት እንድንፈጥርና እንድንጠያየቅ ስለአደረገኝ በግሌም ተጠቃሚ ነኝ::

አዲስ ኪዳን : አሁንም ወደ አገልግሎት ቡድኑ ልመልስሽ በዚህ የፍቅር ግብዣ ውስጥ ያሉ አገልጋዮች የሚሰጡት አገልግሎት እንዴት ነው?

አበበች/አቡ : አሁን ያለው የአገልግሎት ህብረት ደስ ይላል:: አገልግሎቱም በመገልገል-: በማገልግል; በማስተናገድም -: ተስተናጋጅ በመሆንም; ቤተሰባዊ ክርስትያናዊ ፍቅር ያሳያል::

አዲስ ኪዳን : ይህ አገልግሎት ለተጠቃሚው መንፈሳዊ ዕድገት እንዴት እረዳቸው ትያለሽ?

አበበች/አቡ : በጣም ጠቅሟል እላለሁ:: ወገኖች እርስ በእራስ መቀራረብን ፈጥሯል ምክንያቱም የምላ ጊዜ ስለሆነ -: ሰፊ ሰዓት አለው ያወያያል -: ያጨዋውታል ፍቅርንም ያመጣል ብዬ አምናለሁ:: ጥሩ ጊዜ ነው::

አዲስ ኪዳን : ለአምልኮ የተሰበሰበው ብዙ ህዝብ ውጤታማ ቀጣይ የተሻለ እንዲሆን ምን ትያለሽ?

አበበች/አቡ : በእግዚአብሔር ፊት በቅድስናና በታማኝነት መመላለስ በሰው ፊትም በትህትና በፍቅር መኖር በዝቅታም በከፍታም እግዚአብሔርን በማመስገን ወደተሻለ ሕይወት ያመጣል እላለሁ::

አዲስ ኪዳን : ለዚህ አገልግሎት የሚጸልዩ ወገኖችን እንዴት ነው የምትገልጭያቸው?

አበበች/አቡ : በፍቅር ነው የምገልጻቸው በጣምም እወዳቸዋለሁ:: እግዚአብሔር ይባርካቸው ተግዳሮት ቢኖርም በጸሎት ይታለፋል የዚህም አገልግሎት የስድስቱ የቡድን መሪዎች ተገናኝተንም በህብረት እንጸልይ ነበር::

አዲስ ኪዳን : ሌላ የምትይው ምን አለ?

አበበች/አቡ : ይህ የፍቅር ግብዣ ከቅዱስ ቁርባን በኋላ መሆኑ ልዩ ውበት አለው:: ሁሉን ያሳትፋል እንጀራ ከመቁረስ ባለፈ ሃሳብን እንከፋፈላለንና ስለ ፍቅር ግብዣ በሐዋርያት ስራ ምእራፍ 2 ቁጥር 42 -47 የሚለው አለ አንብቡት::

አዲስ ኪዳን : ያጋጠሙ ችግሮች አሉ?

አበበች/አቡ : ያጋጠም ችግር የለም ሁሉም ደስተኛና ፈቃደኛ ነው::

አዲስ ኪዳን : አመሰግናለሁ::

አበበች/አቡ : እኔም አመሰግናለሁ::

ቃለ ምልልስ

## በአገልግሎት ዙሪያ ከወንድም ግርማ ተበጀ ጋር የተደረገ ቆይታ

አዲስ ኪዳን : ስምህን ማን ልበል?

ወንድም ግርማ : ግርማ ተበጀ::

አዲስ ኪዳን : በቅድሚያ ለቃለ ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆንህ አመሰግናለሁ::

ወንድም ግርማ : እኔም ስለተጋበዝኩ አመሰግናለሁ::

አዲስ ኪዳን : እስቲ ከልጅነትህ እንጀምር:: የት ተወለድክ የት አደክ የትስ ተማርክ?

ወንድም ግርማ : ከእናቴ ከወይዘሮ በላይነሽ ደስታና ከአባቴ ከአቶ ተበጀ አሊጋዝ በወሎ ክፍለ ሃገር በራያና ቆቦ ከተማ ተወለድኩ:: አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴንም በቆቦ ተማርኩ; ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ወልድያ ጨረስኩ::

አዲስ ኪዳን : ወደ መንፈሳዊ ሕይወትህ ልምጣ; ወደ ጌታ እንዴትና መቼ መጣህ?ወንድም ግርማ : ታህሣሥ 2 ቀን 1974 ዓ.ም. ወልድያ ከተማ ለእረፍት ከመጣች የዩኒቨርስቲ ተማሪ ብርሃን መንፈሳዊ መጽሄት አግኝቼ ነው የጌታ ቤት አጀማመሬ::

አዲስ ኪዳን : እስኪ ዘርዘር አድርገህ ልትነግረኝ ትችላለህ?

ወንድም ግርማ : አዎ በዚህ የብርሃን መጽሔት ውስጥ ስለ ምስክርነት በፓስተር ዳንኤል መኮንን በቀረበ የፈውስ ምስክርነት ልቤ ተነካ:: በእዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ፓስተር አሰፋ ጉግሳን በአጋጣሚ አገኝሁት (አሁን ያለው ሳንዲያጎ ነው) እባክህ ማህበራችሁ ውስጥ አስገባኝ የሚከፈልም ክፍያ ካለ እከፍላለሁ አልኩት:: ፓስተር አሰፋም ፈገግ ብሎ ክፍያ የለውም ያለውኝ አስታውሳለሁ:: በዮሐንስ 3;16 ላይ ያለውን ክፍል ጠቀሰልኝ:: እንዲህ ይላል "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለአለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና" በማለት ልቤን የበለጠ አነሳሳው:: እኔም ለእራሴ ቃል ገባሁ የገባሁትም ቃል ወደ አማኞቹ በመሄድ ለመጸለይ ነበር:: እንግዲህ መጽሔቱን ካገኘሁ በኋላ የገባሁትን ቃል በመርሳት ለሁለት አመት ቆየሁ:: እግዚአብሔርም በህልም አስታወሰኝ:: እኔም በህልም ለአሳየኝ እግዚአብሔር ታዘዝኩኝ:: በእንዲህ ሁኔታ ነው የጌታ ቤት አጀማመሬ::

አዲስ ኪዳን : ጌታን ያገኘኸው አገራችን በኮሚኒስት ሥርዓት በነበረችበት ጊዜ ነው-; እና እንዴት ነበር መንፈሳዊ ሕይወት? ያመቻል? ችግር አልነበረውም?

ወንድም ግርማ : (ሳቅ … ተከዝ) አዎ ዘመኑ ጥሩ አልነበረም በተወለድኩበትና በአደኩበት ከተማ ግርማ ጴንጤ ሆኗል ተብሎ ተወረቶ ስለነበረ ወጣቱን ይበክላል ተብዬ እስራትና ዕንግልት ገጥሞኛል::

አዲስ ኪዳን : ታዲያ እስራቱ አስደነገጠህ?

ወንድም ግርማ : አዎ ፈርቼ ከጸሎት ቤት እቀር ነበር:: ይሁንና በህልም ያገኘሁት ጌታ ያበረታኝ ነበር::

አዲስ ኪዳን : እና በዚህ ሁኔታ ነበረ አጀማመርህ?

ወንድም ግርማ : አዎ! ጌታን ባወቅሁ በሶስተኛው አመት ወደጅማ ሔድኩ: ዘመኑም 1977 ዓ.ም. ነበረ:: በፓስተር ጌዴዎን ተስፋዬ የደህንነት ትምሕርት ተምሬ የውሃ ጥምቀት ወሰድኩ እግዚአብሔርም በመንፈስ ቅዱስ ሞላኝ :: ከዚያም ወደ ወሎ ተመልሼ በፆምና በጸሎት እየተጋሁ አገልግሎት ጀመርኩ::

አዲስ ኪዳን : ምን ነበር አገልግሎትህ?

ወንድም ግርማ : የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ነበር::

አዲስ ኪዳን : አገልግሎት ስትጀምር ስደቱ ቆመ?

ወንድም ግርማ : አልቆመም እንዲያውም በረታ:: ስድስት ወር ተፈረዶብኝ ወህኒ ቤት ገብቼ ፍርዱን ሳልጨርስ በሶስት ወር ተፈታሁ:: ተፈትቼም በአገልግሎት እየበረታሁ እግዚአብሔርም እያረዳኝ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ብዙ ነፍሳት ይጨመሩ ነበር:: በዚህ የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ለአራት ዓመት ቆየሁ::

አዲስ ኪዳን : ከአራት ዓመት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት በኋላስ?

## ቃለ ምልልስ

# ከወንድም ግርማ ተበጀ ጋር ...

ወንድም ግርማ : ደሴ ባለችው የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ከ1981 -1991 አገለገልኩ ከ1991-1995 ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ሣር ቤት ሙሉ ወንጌል በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎ ቆየሁ::

አዲስ ኪዳን : ምን ምን ነበር አገልግሎትህ?

ወንድም ግርማ : በመስበክ; በመዘመር; ደህንነት በማስተማርና የምክር አገልግሎት ነበር::

አዲስ ኪዳን : እንደገና ወደ ግል ህይወትህ እንመለስ:: አሜሪካ እንዴትና ምቼ መጣህ?

ወንድም ግርማ : ጌታ ተናግሮኝ ነበር እናም እየጠበቅሁት ነበርና በ2003 እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር ዲቭኢ ሎተሪ ወጣልኝና ወደአሜሪካ መጣሁ::

አዲስ ኪዳን : ታዲያ አሜሪካንን እንዴት አገኘሸው?

ወንድም ግርማ : በጣም ጥሩ ነው:: እንደዛ ስልህ አሜሪካ ጽድቅም ጽድቅም ያለሆነ ይስተዋላል::

አዲስ ኪዳን : እና መንፈሳዊ ሕይወትህን አላዛለውም?

ወንድም ግርማ : የለም የለም በጭራሽ በጸጋዬም በአገልግሎቴም ምንም አልጎደለም:: እዚህ ያመጣኝም እግዚአብሔር አልተሳሳተም::

አዲስ ኪዳን : በአሜሪካን አኗኗርህ አገልግሎት እንዴት ነው?

ወንድም ግርማ : መልካም ነው እየሰራሁ በጸሎትና በመስበክ አገለግላለሁ:: የእግዚአብሔር ቃልም በ1ኛ ተሰሎንቄ 2-:9 ላይ እንዲህ ይላል "ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሰራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበከን" ነውና በዚህ ቃል እውነት እመላለሳለሁ::

አዲስ ኪዳን : ልንጨርስ ነው ይኼ ቀረ ይህን ባልኩ የምትለው አለ?

ወንድም ግርማ : አዎ አሜሪካ ጫካ ነው:: ኑሮዬ ብቻ ካልክ ትዋጣለህ:: አንዳንዶች ክርስትና ቀላል ነው ይላሉ ሌሎቹ ከባድ ነው ይሉታል: እኔ ግን የምረዳው ክርስትና መኖር ነው እላለሁ:: በሰበኩት በዘመሩት የዕለት ተዕለት ኑሮ እንደ ቃሉ መውጣትና መግባትን ይጠይቃል:: አሜሪካም ፅድቅም ሐጢአትም የተትረፈረፈበት አገር ነው:: በወሰንከው መሔድ የአንተ ድርሻ ነው:: ኢየሱስን ወደ መምሰል የሚያመጣ ኑሮ ግድ ነው-: የማያመቹ ነገሮች ቢኖሩም ችሎና ታግሶ በትህትና በፍቅር መመላለስ ይገባል -: አገልግሎት ዋጋ ቢያስከፍልም እጥፍ ድርብ ክብር አለው:: አምላኬም በዝቅታም በከፍታም ባለፍኩበት ሁሉ አብሮኝ ስለነበረ ወደፊትም ስለሚኖር ፍቅሩና ምህረቱ ያልተለየኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ:: ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ:: ፊሊጵስዩስ 4:13

እግዚአብሔር ይባርክህ!

## ከአገልግሎት ዘርፍ

### የዝማሬ አገልግሎት

ይሄነው ማሞ ያደቴ እባላለሁ፣ትውልዴ እና እድገቴ አዲስ አበባ ነው፡፡ስለ አገልግሎት ሳስብ በውስጤ የሞላው የእግዚያብሔር ፍቅር ነው። እግዚያብሔርን በጣም እወደዋለሁ ዘመኔን ሁሉ ለእርሱ ብሆንለት ለእርሱ አይመጥነውም ።

የዝማሬዬ ጅማሬና መነሻው በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሲሁን እኔን ያገኘሁት ግን በዝማሬ ውስጥ እየዘመርኩ እንደሆነ አስባለሁ።ታዲያ ስለ ዝማሬዬ አገልግሎት ሳነሳ ከልጅነቴ ጀምሮ እንደሆነና ጌታን እነደአገኘሁም የደህንነት ትምህርት እየተማርኩ የውሃ ጥምቀት እንኳን ሳልወለድ ነው በቤተክርስቲያን አገልግሎት የጀመርኩት፣ አገልግሎቴም በአዲስ አበባ ሙሉወንጌል "ኢዮሳፍጥ" ኳየር ሲሆን ከአስር ዓመት በላይ አገልግያለሁ።አገልግሎቴ በዝማሬ ብቻ አልነበረም ለዝማሬ የሚሆኑ ግጥሞችንም በማዘጋጀት እና በማረም ነበር። እና ምንም እንኳን በዝማሬ አገልግሎት ቆይታ ቢኖረኝም አሁንም ገና ነኝ ገና አልነካሁትም፤ የዝማሬ አገልግሎቴ ብዙዎቹ ያሬዳዊ ሲሆኑ ድራማቲክ የአዘማመር ስልት አዘወትራለሁ ታዲያ ይህ የዝማሬ አገልግሎትበጌታ ላሉም ፡ላልዳኑትም ጠቃሚ እንደሆነ አያለሁ ፣ ብዙዎች በዝማሬዎቹ ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንደተጨመሩ አውቃለሁ ።

ዝማሬ መንፈሳዊ መሳሪያ ነው ፣ ዝማሬ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው።እልፍ አእላፍ መላዕክት ቀን እና ሌሊት በእግዚአብሔር ዙፋን ስር ያዜማሉ ታዲያ የእኔ አገልግሎት ገና እጅግ ገና ነው። ለአምላኬ ያንስበታል ፣ ንጉስ ዳዊት ራቁቴን ባመልከው ብሎ የለም? እናም ለዝማሬም ትልቅ ቦታ አለኝ። ሡርግ ሊታደሙ የመጡ አህዛብ ወገኖቻችን በዝማሬ ተማርከው ወደ ጌታ የመጡ ብዙ ሰዎች እንዳሉ አስታውሳለሁ። በዝማሬ ብዙ ሰዎች ተማርከዋል እኔም ተባርኬያለሁ።

አሜሪካን እንደመጣሁም በአቤኔዜር ቤተክርስቲያን በህብረት ዝማሬ አገልግያለሁ በዚያችም ቤተክርስቲያን ጥሩ ጊዜ ነበረኝ፤ ሳንፍራንሲስኮ አዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን አገልግሎት ስጀምር እጅግ የሚያስደስት ሆኖ ነው ያገኘሁት ። አብረውኝ የሚያገለግሉትም ፍፁም ፍቃደኞች እና ደስተኞች ስለሆኑ የእኔም ደስታ ሁሌ እየጨመረ እና የአገልግሌት ጊዜውን በናፍቆት የምጠብቀው ነው፡፡ የሙዚቃ ዝግጅቱንም እግዚአብሔር በሰጠን ወጣቶች ዳሪዮስ እና ጌዲዮን የደመቀ ሲሆን በእግዚአብሔር ስም ላመሰግናቸው እወዳለሁ። በዚህችም ቤተክርስቲያን ጥሩ ህብረት እና ፍቅር አለ ፡ ለህብረት ዝማሬውም መመስረትና መጠናከር ምክንያት የሆነውን ወንድም እዮብን አመሰግናለሁ፤ ፓስተር ተስፋዬንም ሳልባርክ አላልፍም።

ታዲያ ለዚህ አገልግሎቱ ተግዳሮት የለውም ማለት አይደለም በህይወት ዙሪያ መረጋጋት ባይኖርም የኑሮ ውጣ ውረዱ እንደዋዛ አይታይም ይህን ችግር ዘሎ ነው አገልግሎቱ። ለአገልግሎቴ ዋና ደጋፊዬ እና አበረታቼ ባለቤቴ ስለሆነች ጌታን ስለእርሷ እያመሰገንኩ እባርካታለሁ። እንግዲህ በአገልግሎት ዙሪያ ይህንን ሲመስል ፡ትልቅ ራዕይ አለኝ በዚህችም ቤተክርስቲያን የሚታዩ ምልክቶች እያለሁ ቤተክርስቲያኗ እንደምትስፋፋ እና ለ አካባቢውም ጥሩ ጠቀሜታ እንዳላት ይታየኛል። በዚህ ሀሳቤን ላቁም ወደፊት በግል ህይወቴ ዙሪያ ደግሜ እንደማወራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

ቃለ ምልልስ

## የመገናኛ አገልግሎት አስተባባሪ ድምፅ

ማራናታ በሚል በግል አገልግሎት ውስጥ የመገናኛ አገልግሎትን እሰጥ ነበር። ይህንንም አገልግሎት ሁሉንም ተደራሽ ለማድረግ ፍላጎቱ ነበረኝ ። በዚህም ሀሳብ ውስጥ እያለሁ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ፓስተር ተስፋዬ አገልግሎቴን ያውቅ ስለነበር ይህን የመገናኛ አገልግሎት በቤተክርስቲያን እንድጀምር አበረታታኝ እኔም ፍላጎቱ ነበረኝ እና በደስታ አገልግሎቱን ተቀበልኩ እንግዲህ እንዲህ ነው የጀመርኩት ።

ታዲያ ይህን አገልግሎት በቤተክርስቲያን ሰጀመር በድምፅ ቀረፃ ነበር ይህንንም ስርጭት ለህዝቡ በጥራት ና በነፃ ለማቅረብ ተሞክራል ። የአገልግሎቱ ዓላማም በቤተክርስቲያን በስራ ምክንያት ላልተገኙት አገልግሎቱ እንዳይጓደልባቸው ታስቦ ነው።

ይህ አገልግሎትበዚህ አልቆመም የምስል ቀረፃዎችን አካቶ አገልግሎቱን ለማስፋት ተሞክሯል፡፡ ዛሬ ቤተክርስቲያን የራሷ ድህረገፅ ያላት ሲሆን ባህሪውም ዓለም አቀፍ የአገልግሎት ተደራሽነት እንዲኖረው ተፈልጎ ነው።

እንግዲህ የመገናኛ አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ነው።ዓለም አቀፋዊ ይዘትም ስለአለው  ጥራቱንም  የጠበቀ እና ጥንቃቄ የተሞላ ነው ። የአገልግሎቱ ዓላማ ወንጌልን ለዓለም ማዳረስ ሲሆን በዚህ ትልቅ አደራ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኗ በርካታ ወጣቶችን ያዘጋጀልን ሲሆን ፣ ስርጭቱም መልካም ነው እላለሁ።

አስተባባሪ

## ሥነ ጽሁፍ

## እግረ መንገድ

የብዙ ሰው ድምጽ የሚመስል-: ጫጫታ የሞላበት-: ሁከት-: እርጋታና መደማመጥ ያልሰፈነበት-: ሁሉም የሚፈልገውን ማስተላለፍ እንጂ ሌላውን የማያስተውልበት ከሚመስል የታደመ መሃል በፍቃዴ ሳይሆን በፍቃዱ ስገኝ: እኔም እንደሚጠበቅብኝ በማሰብ የቻልኩትን ያህል ለመጀመሪያ ጊዜ በጩኸት ተቀላቀልኩ::

ከዛ በኋላ በጪሂዎች ስር መውደቄን ያስተዋልኩት በቁጥር ለመስፈር ከሚያዳገቱ አያሌ ሰአታት በኋላ ነበር የባነንኩት:: ሁሉም እንደኔ እየተሸወደ የተገናኘ መሆኑንን አስተዋልኩ:: ሁላችንም ለመጀመሪያ ጊዜ ባሰማነው ድምፅ ስንመሳሰል ለዚያውም እንደ መስፈርት እንደ ተቆጠረብን ከረጅም ጊዜ በኋላ በማወቅም እንመሳሰላለን::

"ምድር መድረክ ናት-: ሰዎችም ተዋናኝ" ያለውን ታላቅ ጸሃፊ አስታወስኩ:: "ሁሉም ትወናውን ሲጨርስ ከመድረኩ ይወርዳል" ብሎ እስከ መውረጃ ጠቁሞናል:: አዎ! እርሱ እስከቻለው ጮኋል:: እሱንማ ጪሂዎች ሲያወርዱት-: እኛም ስናወርድ እናውቃለን::

ከዛስ ብኋላ?

ይህንንም ለሁላችንም እኩል እንደታደለን: ሲወርዱ ባስቆጠሩት ሳይሆን-: በጨረሱት እና በየመቋጫቸው (በየመድረሻቸው) ከመድረክ መውረድ ግዴታ መሆኑን ለማስተዋል ጊዜ ለእኔ እንደፈጀብኝ: በእኩል ሰዓት እየጮህን ከተቀላቀልነው መሃል ብዙዎች እንዳላስተዋሉ አስተዋልኩ::

በመሆኑም መድረኩ ላይ የሚታየው ትዕይንት የተለያየ አይነት ጩኸት የሞላበት ቢሆንም-: ለመረዳት የሌላ እርዳታ እስከተወሰነ ሊረዳ እንደሚችል ይህም እስከ መውረጃው መሆኑን ልቤ ስላወቀው: ከወረድኩ በኋላ ምን እንዳለ የማወቅ ጉጉቴ ግን አሁንም ጩኸቴ ነው::

ወራጅ አለ? ወራጅ? እህ ዓይነት ጥያቄ ይሁን ትዕዛዝ በየሰኮንዱ የሚሰማ የመድረኩ መቆጣጠሪያ አሰራር መሆኑን አስትዋልኩ, ግና ይህ ጩኸት ከየት እንደሚመጣ ባላውቅም: ነገር ግን ትወናቸውን የጨረሱት በግል ሰምተው ምላሽ የሚሰጡበት የጠቢቡ ጥበብ መሆኑን ለማስተዋል ጓጓሁ: ግን አንድ ጥያቄ በዐእምሮዬ አለፈ "ምን አለበት! ለሞላ መድረክ እኔ ሳልሰማ ከሚያወርዳቸው: እያሸጋሸገ መድረኩ ላይ ቢቆዩ"? አልኩ በልቤ:: ለካስ ይህ የስንፍና ጩኸት ነው የትወናውም ማለቅ ከመድረኩ በድርቅና ሆነ በልመና ከመውረድ ማስረዘም ይቻል ይሆን እንጂ: መውረድ ግድ ነው::

ለቆጣሪው ሳይሆን ለተቆጣሪው ምን ያህል በራስ ጥያቄና አነሳሽነት ከመድረክ ለመውረድ የነበረ የፍላጎት ጩኸት በመድረኩ ላይ ቆጥሮ ያሳፈረ እና የፈቀደ የእርሱ ፈቃድ ሁሉን ትገዛለችና; ለመውረድና ላለመውረድ የቆጣሪው ጩኸት እንደተሰማ :- ተከትሎ የሚሆነውን ለሰነፍ ካልሆነ ለሁሉ ግልጽ ነው::

አሁንም ትዕይንታቸውን የጨረሱ ወዴት እንድሚሄዱ ለማወቅ ያለኝ ጉጉት ብሷል:: ምክንያቱም በታሪክ አንድም ጨርሶ የወረድ ተመልሶ አያውቅም በርግጥ የጨረሱ መስሏቸው: በሰው ተራ ይሁን በመደናቀፍ ከመድረኩ ወርደው ሳይሆን ወድቀው የነበሩ ተመልሰው በድንግዝግዝ ያዩትን ጮኸዋል::

ይኼ መድረክ የያዘውን ጉድ እና የሚያሰማውን የጩኸት ዓይነት ለመዘርዘር ጊዜ ለጊዜ መስፈሪያ እንዳለው አስተዋልኩ:: በመድረኩ ላይ ባለ እጣ የሆነው የመጀመሪያ ትኩረቱ : ተዋንያናቱ ሁሉም

*ሥነ ጽሁፍ*

# እግረ ....

ሁለት ብርሀን የምያወጡ ቀዳዳዎች ከወደላይ እንዳሏቸውና እንድ አንዴ ቀይ: ጥቁር , ነጭ ብቻ ዐይነት:: በጎንና በጎን ካሉ ቀዳዳዎቻቸው እንደሚገባው የጩኸት ብርሀን ያመነጫሉ:: የሚገርመው እንደሚያመነጩት የብርሀን ፍንጣቂ ተመልሶ ወደቀዳዳዎቹ የሚመጣው ምላሽ ይለያል:: ይህ ነገር መድረኩን አንድ አንዴ ሲያሳምረው አብዛኛውን ጊዜ ግን በዝብርቅርቅ በማይገባ በማያምር ብርሃን ይሞላዋል:: ከነኝህ ቀዳዳዎች በታች ሌላ የሚያስገርመው በሚያስገባው ሳይሆን በሚያወጣው ጥቁርና ነጭ ቀይ ሰማያዊ ውፍራም ቀጭን ሰቅጣጭ አሳዛኝ አስደሳች ፈዋሽ ወዘተ ከሚባሉ ዝርዝሮች በሚዘረጋ የጩኸት ገመድ ዓለምን ዞሮ የመመጣ ባለችሎት እንዳለ ተመለከትኩ:: በነኝኹ ቀዳዳዎች ከሚገባውና ከሚወጣው ጩኸት የተነሳ እያንዳንዱ ተዋናኝ የተለያየ ቅርፅ አውጥቷል:: ሖደ ሰፊ ሳይሆን ሆዳም በራስ ቅሎቻቸው ብዙ ልዩነት ባይኖርም የተዘብራረቅ ጩኸት የተሞሉ ስለሆኑ ትከሻው ላይ በተቀሰሩት እንዝርቶች ምን ዓይነት ድውር እየደወሩ ከወገቡ በታች ባሉት ሁለት መገተሪያዎች ላይ ተሳፍሮ ሲታይ መያዝ የማይገባውን የተሸከመ የሩቅ መንገደኛ እና በዝብርቅ ጩኸት የሚንገላታ ተዋናኝ የተለመደ ነው :: መድረኩም እንደሆነ / እንደተሞላ አስተዋልኩ::

አሁንም ከመድረክ በኋላ ወዴት ነው የሚኬደው የሚለውን ጩኸት እኔም በዚሁ መድረክ ላይ ሆኜ ተደመምኩ::

ከመድረኩ መግቢያ እስከ መውረጃ መጓዜ አይቀርም ትዕይንቴን አስጨኬ ለመውረድ ያለኝ ጊዜ በጣም አጭር ነው:: ስለዚህ ስወርድ ወዴት እንደሚሄድ የሚያስረዳኝን ፍለጋ ጩኸቴን አቀለጥኩት መድረኩን የረበሸኩ መስሎኝ ነበር:: ለካስ የትዋኔው ክፍል ነው:: ከመውረዴ በፊት ወደ መውረጃዬ እየሄድኩ እግረመንገዴን ነበር ያሰማሁት:: ማንም የለም የሚያስረዳህ ከየት እንደመጣህ ብታውቅ ወዴት እንደምትሄድ ታውቅ ነበር የሚል ጩኸት በመድረኩ በሙሉ አስተጋባ:: የሚገርመኝ በመድረኩ ከሚተወኑ አብዛኞቹ በየቀዳዳዎቻቸው ከሚገባውና ከሚወጣው ግበብስብስ ጩኸት የተነሳ ሆዳቸው አብጦ አንገታቸው ዞሮ የራስ ቅላቸው ከብዶ ስመለከት ከተሸከምኩት ኮተት የትነሳ የልብና የሆድ ዕብጠታቸው አስገረመኝ እንዲህ ላለ ያስረዱኝ ጩኸት ከማየው ነገር የተነሳ ከየትም በጎ ጩኸት አልሰማምና መውረዴ ላይቀር እግረመንገዴን እኔም ላግበስብስና ልመሳሰል ጮኹ ከኋላዬ በሚበልጥ ጩኸት ከወዴት እንደመጣሁና ወዴት እንደምሄድ አውቃለሁ የሚለውን ጩኸት ሰማሁና

ከመንግዴ ዞር አልኩ ዮሐንስ 8:14

"ተራራ መውጣት ቁልቁልት መውረድ

ዓይኔን አድከሞት የጽዮን መንገድ

ዛሬስ አበቃ የኔ ነገር ስል

ጌታዬ ደርሶ አወጣኝ ከእስር"

ወንድም ኢዮብ አበበ

# እንግዳችን (ማርቆስ 4:1-20)

## ይህ ምሳሌ ዘላቂ ፍሬ ለማፍራትና ዘላለማዊ ርስትን ለመውረስ ምን አይነት የሕይወት ልምምድ ያስፈልጋል ብለን ብንጠይቅ መልስን የሚሰጥ ይመስለኛል::

ጌታ እንዳስተማረን ዘሩ የእውነት ቃል ሲሆን ማሳው የሰው ልብ ነው:: እንግዲህ ዓራት ዓይነት ልብ ከዓራቱ ማሳዎች ጋር እንዴት ይማሰላል? ይህን ለማብራራት እንሞክር::

1) የመጀመሪያው ማሳ የመጓጓዣ መንገድ ላይ ተተክሏል :: እንግዲህ ፍሬው ለዘር እንኳን ሳይበቃ በወፎች ተለቅሞ ይጠፋል:: ያልተዘጋጀ ልብ ለሰይጣን ክፉ ስራ የተጋለጠ ነው:: በቀላሉ ከሕይወት መንገድ ለመራቅና ለመታለል ያጋልጠናል:: ይህ ልብ በጨለማ ውስጥ ስላለ ምንም ብርሃኑ ቢበራም ከብርሃኑ በመሸሽ በጨለማ ውስጥ ይኖራል:: "ብርሃን ወደ ዓለም መጣ ሰዎች ግን ጨለማን ወደዱ" ብሎ ቅዱስ ዮሓንስ ጽፏል:: ጴንጤናዊው ጲላጦስ በጌታ ላይ ሊፈርድ በቆመ ጊዜ የእውነትን ቃል ለመስማት እድል ቢኖረውም ግን ቆም ብሎ ምን እንደሰማ ሳያስተወል የጌታ ፈራጅ ሆኖ ስሙ ለዘላለም ይወቀሳል:: (ወንጌል, ጸሎተ ሃይማኖት)

2) በጭንጫ (ድንጋይ) ላይ የወደቀው ፍሬ ደግም ሰምተው ለጊዜው ደስ ብሏቸው ይቀበሉታል:: ነገር ግን በቃሉ ምክናያት መከራና ስደት በሚመጣ ጊዜ በቶሎ ይሰናከላሉ:: እነኝህ ሰዎች ምናልባት ወደ ጌታ ሲመጡ ዐንድን ነገር ፈልገው ይሆናል:: ጌታም ተዓምራትን ሰሪ አምላክ በመሆኑ ድንቅን ዓድርጎላቸውም ይሆናል:: በጌታ ከተፈወሱት በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩት መካከል ምን ያህሉ አብረውት እስከ መስቀሉ ሄዱ? ሆዳቸው ሲሞላ መሲህ ነው ብለው ሊያነግሱት ከተነሱት መካከል ስንቶች በመከራው ጊዜ ጥለውት የጠፉት ወይም ስቀለው ብለው የጮሁት? ምናልባት ደግሞ የፈለጉት የጌታን በረከት እንጅ የጌታን መንገድ መስቀል መሸከምም እንዳለ በመረዳት ዐይመስልም:: ብዙዎቻችን በጌታ አስራር ግር የሚለን በዚህ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ይመስለኛል:: የጌታን የተስፋውን ቃል ስናነብ በልባችን እጅግ ደስ ይለናል:: የጌታ ሀዋሪያት ሁሉ በዚህ ፈተና ዓልፈዋል:: በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ከመሞላታቸውም በፊት እጅግ ካስቸገራቸው ነገር ዋናው የሚመስለኝ ስለ ጌታን መከራን መቀበል ምናልባትም የመከራውም ምክንያት የገባቸውም አይመስልም:: መከራን መካፈል ቢፈልጉም ስጋቸው ለመታዘዝ ሲያቅተው እናያለን:: ልባቸው ክብርን ብቻ ሊቀበል ተዘጋጅቶ ነበር:: በአሁኑ ዘመንም እንዲሁ ብዙዎች ወደ ጌታ ሲመጡ የተሰበከላቸው የጌታ ስጦታ ብቻ ከሆነ : በጌታ ፈቃድና ስለ ስሙ መከራ ሲመጣ በጌታ እንደሚያዝኑ ይሰማኛል:: ቅዱስ ኢዮብ ግን "ምንም ስጋዬ ቢፈርስም መድሃኒቴን በዓኔ ዓየዋለሁ" ብሎ ጌታን በመከራው ጊዜ አከበረው::

ከቅዱስ መጽሓፍ ታሪክ ዘወር ብለን ስናይ ከግብጽ ከውጡት እስራኤላውያን ከሁለት ሰዎች በስተቀር ማንኛቸውም ወደ ከንዓን ሊገቡ እንዳልቻሉ እንረዳለን:: (1ኛ ቆሮንቶስ 10:1-13; እብራውያን 3:1-18; እብራውያን 4:1-2) እነኝሁ ሁሉ የእምነት ጉዞአቸውን የጀመሩት በታላቅ ደስታና ሆታ ሲሆን ግን ወዲያውን የግብጽን መሬት ሳይለቁ ማጉረምረም ጀምረው ነበር:: ቅዱስ መጽሃፍም ልባቸው ከድንጋይ ይልቅ እንደሚጠጥር ሲያስመለክት እግዚአብሔር አሰርቱ ቃላትን በድንጋይ ላይ ጽፎ ለሙሴ እንደሰጠው ይናገራል::
" አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።" ትንቢተ ሕዝቅኤል 36:26 ብሎ መንፈስ ቅዱስ ተናግሯል:: የተዘራው ፍሬ በድንጋይ ላይ እንደማይበቅል ሁሉ እንዲሁ ጌታን በትእግስት ጠብቆ መኖርን ያልለመደ ዓማኝ ወደኋላ ለመመለስ እንደሚፈተን ይሰማኛል::

3) ሶስተኛው ዓይነት ልብ ደግሞ በመልካሙ የእግዚአብሔር ስጦታዎች በመታለል እነርሱን እንደ ግብ በማድረግ

# እንግዳችን ...

ሕይወቱን ይጨርሰዋል። እነኝህ መልካሙ የእግዚአብሔር ስጦታዎች እንደጣኡት በመሆን ልቡን የሚያልፍ በሆነው ነገር ይሞላዋል። የእግዚአብሔር ቃልን ከመጠማት ይልቅ የምድርን ሓብት መመኘት ይሻቸዋል (1ኛ ጢሞቴዎስ 6:6-12, ፊሊጵስዩስ 3:17-21; ኤፌሶን 5:1-12) በእስራኤል መሳፍንት ዘመን ጌታ ከከንዓን ያጠፉቸው አሕዛብን እንደመሰሉ በመጽሃፈ መሳፍንት ምእራፍ 19 እና 20 እናነባለን። እንዲያውም ምእራፍ 1 ላይ እስራኤል ከከንአን ሕዝብ ሲዋጋ ምእራፍ 20 ላይ ደግሞ እርስ በርስ ሲዋጉ እናያለን። እስራኤል ተከፍሎ ከንዓን ሆኖ ተገኘ። በችግራቸው ጊዜ ወደ አምላካቸው ይጮሁና በለምለምና በበረከት ጊዜ ትተውት ይነጉዳሉ።

4) መልካሙ ልብ ግን በጊዜውም ኣለጊዜውም በጌታ ጽድቅ ታምኖ ለፍቅሩ ተገዝቶ አምላኩን ጠብቆ የሚዘልቅ የእምነት ጀግና ዘላለማዊውን አይቶ ጊዜያዊውን ንቆ በዚህ አለም እንደ መጻተኛና እንግዳ ሆኖ ስለቅዱስ እግዚአብሔር ሲል መከራን ተቀብሎ ያልፋል።

እንግዲህ ሕይወታችንን ለጠራን አምላክ ሰጥተን በትዕግስት ተጉዘን የአምላክን ቃል እንደ መና እየተመገብን ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ጉዞአችንን እንቀጥል። ዘላለማዊውን ፍሬ በአውነት እንድናፈራ ለጠራን ልወደደን በደሙም ከሃጢያታችንም ላጠበን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመታዘዝ ስጋን አለምንና ሰይጣንን በመካድ አምላካችንን እናክብር።

መዝሙረ ዳዊት 1:2 ላይ ጻድቅ በአግዚአብሔር ህግ ደስ ይለዋል። ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያሰላስለዋል። ብሎ ይናገራል። ከዚህ አለም ርኩሰት ለማምለጥ ጌታችን ታላቅ ከቡርና ውድ የሆኑ ተስፋ ቃላት እንደሰጠን ቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛው መልእክቱ ምእራፍ 1 ቁጥር 4 ላይ ያስተምረናል። በዚህ ምድር ስንኖር ሰይጣንን የምናሸንፈው በምስክርነታችንና በጌታ ደም ሲሆን፣ ጌታ መንፈስ ቅዱስን እንዳናሳዝነው ትህትናና ምህረትን እንዲሞላን እጸልያለሁ።

በዶ/ር መዓዛ መኩሪያ

እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

የዮሐንስ ወንጌል

ምዕራፍ 14 : 6

# 2014

**January**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | |

**February**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | |

**March**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | 31 | | | | | |

**April**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | | | |

**May**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 |

**June**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

**July**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | | |

**August**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | | | | | | |

**September**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | | | | |

**October**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | |

**November**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | | | | | | |

**December**

| S | M | T | W | T | F | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | 31 | | | |

**January**
20: Martin Luther King Day

**February**
14: Valentine's Day
18: Presidents' Day

**March**

**April**
18: Good Friday
20: Easter Sunday

**May**
11: Mother's Day
26: Memorial Day

**June**
15: Father's Day

**July**
04: Independence Day

**August**

**September**
01: Labor Day

**October**
13: Columbus Day
31: Halloween

**November**
11: Veterans Day
27: Thanksgiving Day

**December**
25: Christmas Day

www.blankcalendar2014.com

## የአዲስ ኪዳን ቤ/ክ ሳምንታዊ ፕ/ሮገራሞች

ዘወትር እሁድ 10፡30am- 12:30 pm

ፀሎት

አምልኮ

ቃል

የህብረት ጊዜ

ዘወትር ማክሰኞ 7፡00pm - 9:00 pm

ፀሎት

አምልኮ

ምስክርነት

**አድራሻ**

**745 Buchanan Street ,**

**San Francisco CA 94102**

**January 5,2014**